# በስደት ሱደን የሚኖሩ ወገኖቻችን ከፍተኛ ግፍ እየተፈጸመባቸው ነው

**ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**
**መስከረም** 11 **ቀን** 2001 **ዓ.ም**. ( September 21, 2008 )

**የወያኔ/ኢሕአዴግ ገዥ ቡድን ከሱዳን መንግሥት ጋር ባደረገው የድብቅ የድንበር መሬት ማስረከብ ስምምነት መሠረት ፤ የሱዳን ጦር የሃገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በመድፈር ወረራ ማድረጉንና ብዙ ጥፋት መፈጸሙ የሚታወስ ነው። ይሁንና ከግንቦት እስከ ሰኔ** 2000 **ዓ.ም. አጋማሽ ባለው ጊዜ ውስጥ በድንበሩ አካባቢ የሚገኙ ወገኖቻችን ባካሄዱት ከፍተኛ የሞት ሽረት ትግል ወራሪው ጦር ቢያንስ የክረምቱን ወራት ከመጣበት የሱዳን ካምፕ ተመልሶ እንዲከርም አድርገውታል።**

**በዚሁ በድንበሩ ሳቢያ በተፈጠረው ግጭት የሱዳን ወታደሮች ሽንፈታቸውንና ውርደታቸውን የተበቀሉት ለረጅም ዓመታት በምድረ ሱዳን ውስጥ በስደት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ መሆኑን ከአሁን በፊት ገልጸናል። በዚሁ በመቀጠል በቅርቡ በደረስንባቸው አስተማማኝ መረጃዎች መሠረት ፤ በሚከተሉት የድንበር ከተማዎች በሸማግሌ ፣ በወጣቶች ፣ በሴቶችና በሕጻናት ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን ግፍ መጥቀስ ያቻላል ፥**

1**ኛ/ በባሶንዳ ከተማ ፥**

**ሀ/ የተገደሉ ወገኖቻችን ፥**

**ማንነታቸው በውል ያልታወቁ** 7 **ኢትዮጵያውያን በሱዳን ወታደሮች ተገድለው ተጥለው ፤ የአከባቢው ሕዝብ ሬሳቸውን ሰብስቦ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበሩ አድርጓል።የእነዚህ ወገኖቻችን ማንነት ያልታወቀበት ምክንያት ባሶንዳ የድንበር ከተማ በመሆኗ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከሱዳን ወታደሮች ጭፍጨፋ ለማምለጥ ሲሉ የሚሸሹባት መተላለፊያ ከተማ ስለሆነች እነዚህ** 7 **ወገኖቻችን ደግሞ ሸሽተው ከመጡት አዲስ መጤዎች መካከል በመሆናቸው ነው።**

**ለ/ የተደበደቡና ንብረታቸው የተዘረፉ ፥**

**ከበርካታ ወገኖቻችን መካከል ስማቸውን ለጊዜው ለማግኘት የቻልነው ፥**

1**ኛ/ ወ/ሮ ሥለዓይኗ ሰማኸኝ**
2**ኛ/ ዮሐንስ ወልደ ማርያም**
3**ኛ/ ወ/ሮ አበባ ጌትነት**
4**ኛ/ አበሩ ብርቄ**
5**ኛ/ ውብት መስፍን**
6**ኛ/ ማሩ ዘገዬ**
7**ኛ/ አታላ መሐመድ**
8**ኛ/ ወ/ሮ አበቡ ዋሴ**
9**ኛ/ ጧፋ ኪዳነ**
10**ኛ/ መልኬ ዳግጤ**
11**ኛ/ እማሆይ ወ/ማርያምና የ**18 **ወራት ልጃቸው ሕጻን ይበልጣል አዳነ ይገኙበታል።**
( **እማሆይ የሚለው ስም በአካባቢው የመጠሪያ ስም ነው።** )

2ኛ/ ወደል ሕልው በተባለው ትንሽ ከተማ ፥

1ኛ/ ነሐሴ 2 ቀን 2000 ዓ.ም. አራት ( 4 ) ኢትዮጵያውያን
2ኛ/ ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም. ዘጠኝ ( 9 ) ኢትዮጵያውያን አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ በሱዳን ወታደሮች ተገድለው ተጥለዋል።

ይህን ዘግናኝና አሰቃቂ ግድያ የሰሙ የአካባቢው ኢትዮጵያውያን ለሕይወታቸው ሳይፈሩ የሞቱትን 13 ወገኖቻቸውን ሬሳዎች በየቦታው ሰብስበው ቀብረዋል። የሟቾቹን ወገኖቻችን ስም ዝርዝርና ሌሎችን ጉዳዮች በመጣራት ላይ ነው።

3ኛ/ ተንዳባ እና አዋታ በተባሉት የድንበር ከተማዎች ፥

ነሐሴ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ሁኔታ 12 ኢትዮጵያውያን ከሚሰሩበት ቦታ ተይዘው እስር ቤት ከቆዩ በኋላ ፤ ከእነርሱ መካከል 2ቱ ሲፈቱ ፤ አስሩ ( 10 ) ግን ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. ከሱዳን እንዲባረሩ በፍርድ ቤት ተበይኖባቸዋል።

እነዚህ 10 ወገኖቻችን በምን መንገድ ከሱዳን እንዲባበሩ እንደተፈለገ በማጣራት ላይ ነን። እንዲባረሩ ከተፈረደባቸው 10 ሰዎች መካከል የ7ቱ ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው ፥

1ኛ/ አቶ ሺፈራው
2ኛ/ አቶ ሙሉ ዓለም
3ኛ/ ዮሴፍ
4ኛ/ አቶ አብዱ
5ኛ/ አቶ መሐመድ አህመድ
6ኛ/ አቶ አታክልት
7ኛ/ ጀማል

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሆይ!

ድንበሩን አስመልክቶ በተከሰተው ግጭት ምክንያት የሱዳን ወታደሮች በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ይሁን በምድረ ሱዳን ውስጥ ባሉ ወገኖቻችን ላይ የሚያደርሱት ግፍና ጭቃኔ ለሕሊና የሚዘገንን ነው። እኛ በመረጃ አሰባሰብ የደረስንባቸው ቦታዎችና ያቀረብናቸው መረጃዎች የችግሩን በጣም አነስተኛ ክፍል ብቻ የሚወክሉ መሆናቸውን ከወዲሁ ማስገንዘብ እንፈልጋለን። በተጨማሪ በአንክሮ ማሳሰብ የምንፈልገው የክረምቱ ወራት ሲያልፍ ድንበሩን ነቅቶ በመጠባበቅና በመከላከል ላይ ያለው ወገናችን እስከ አፍንጫው በታጠቀው በወያኔና በሱዳን ጣምራ ጦር ጥቃት ሊደርስበት እንደሚችል ነው።

በወገኖቻችን ላይ ለደረሰውና ለወደፊትም ለሚደርሰው ግድያ ፣ ንብረት መዝረፍና ማውደም ፣ እሥራትና ድብደባ ተጠያቂ የወያኔ ገዥ ቡድንና የሱዳን መንግሥት ሲሆኑ ፤ በተለይም ደግሞ አቶ መለስ ዜናዊና ፕሬዝዳንት አል-በሺር በዋናነት ተጠያቂ ናቸው። በወገኖቻችን ላይ የሚፈጸመውን ጭፍጨፋና ግፍ በተጨባጭ ማስረጃዎች እየተከታተልን የዓለም-አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች እንዲያውቁት የምናደርገውን ተግባር እንቀጥላለን። ለዚህም ፤ የማንኛውም ሃገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ ትብብር እንጠይቃለን።

የሃገራችን ዳር ድንበር በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ